# ታሪክና ጥበብ በአምባሳደር ህላዌ ዮሴፍ ሲዳሰስ

**ሲሳይ መንግስቴ አዲሱ**

የመጽሀፉ ርዕስ፡ ታሪክና ጥበብ-የግጥም መድብል፣
የመጽሀፉ ደራሲ፡ አምባሳደር ህላዌ ዮሴፍ (ታጋይ)፣
የታተመበት ጊዜ፡ 2007 ዓ.ም፣
አሳታሚ፡ ሴንትራል ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ

ስንቶች ተኮላሽተው ከእሮንቋው ዘቀጡ፣
ስንቶች ተቸንፈው ከጎዳናው ወጡ፣
ጥቂቶች ቆራጦች ያልተንበረከከነው፣
ነገ እልፍ እንሆናለን ታሪክ ምስክር ነው፡፡
ታጋይ ህላዊ ዮሴፍ 1975

**መንደርደሪያ**



እንዳያልፉት የለም ያ ሁሉ ታለፈ፣ ታጋይ የህዝብ ልጅ በደሙ በላቡ ደማቅ ታሪክ ጻፈ፡፡ የሚለው የኢህዴን-ብአዴን የትግል መዝሙርም በታጋይ ህላዊ ዮሴፍ ተደርሶ ዜማ ተዘጋጅቶለት በሁሉም ነባር የኢህዴን ታጋዮች ብቻ ሳይሆን በነጻ መሬት አርሶ አደሮች ዘንድ ሳይቀር በፍቅር ይዜም እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ ታጋይ ህላዌ ዮሴፍም ከጥቂቶች ቆራቶች ካልተንበረከኩት መካከል ነበርና ያን ሁሉ መከራና ስቃይ አልፎ የድሉ ተቋዳሽ በመሆኑ በእርግጥም ታሪክን እንዲህ በግጥም መልክ አሰናስሎ መከተብ ጀመሯልና በዚህ አጋጣሚ አንኳን ደስ አለህ ማለት እፈልጋለሁ፡፡

የቀድሞው የኢህአፓ ታጋይና የኢህዴን መስራች እንዲሁም ከፍተኛ አመራር የአሁኑ ዲፕሎማት አምባሳደር ህላዌ ዮሴፍ ባለፉት አርባ ያህል የትግልና የድል አመታት ውስጥ ከመላከ ሞት ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቶ ትንቅንቅ የገጠመባቸው ጊዜያት እጅግ በርካታ ሊሆኑ እንደሚችሉ አስቀድሜ ብገነዘብም እኔ በበኩሌ ሁለቱን ከሞት መንጋጋ ያመለጠባቸውን አጋጣሚዎች መቼም ቢሆን ልረሳቸው አልችልም፡፡

ይቅርታ አምባሳደር ህላዌ ዮሴፍን አንተ በማለት ለመግለጽ የደፈርሁት አንድም ታጋይ ስለሆነና እጅግም አድርጌ ስለምወደው ሁለትም ገጣሚና የጥበብ ሰው አንቱ አይባልም የሚል የቆየ በሂል ስላለ መሆኑን አንባቢ ከወዲሁ እንዲገነዘብልኝ መሻቴን መግለጽ እፈልጋለሁ፡፡ በመንደርደሪያ መልክ ወደተነሳሁበት መሰረታዊ ጭብጥ ልመለስና አንደኛው ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከኢህአፓ ጋር ተቀላቅሎ ሲንቀሳቀስ በደርግ ሶሎግ ወታደሮች ተይዞ በግፍ ማዕከላዊ ከታሰረ በኋላ የካቲት 19 ቀን 1969 ዓ.ም ሀምሳ ከሚሆኑ የትግል አጋሮቹ ጋር ለመረሸን ወደ ጫካ በሚወሰዱበት ወቅት ኮተቤ አካባቢ ሲደርሱ በታዕምር ሊባል በሚችል አኳኋን ራሱን ከመኪና ላይ ወርውሮ መሬት ላይ በመጣል እስትንፋሱ እንድትቀጥል ማደረግ መቻሉን በተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ መጽሀፍ ቅጽ አንድ ላይ ይመስለኛል ራሱ በቀጥታ የተረከልን መሆኑ የሚታወስ ሲሆን በዚህ የግጥም መድብል መግቢያ ላይም ክስተቱን በአጭሩ አስታውሶት አልፏል፡፡

ሁለተኛው አጋጣሚ ደግሞ ከድል በኋላ ሊባል በሚችል ደረጃ በ1983 መጨረሻ ላይ የኢህዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ባህር ዳር ከተማ ላይ ባካሄደው ስብሰባ ይርጋ አበበ (ሀው ጃኖ) ይዞት በነረበው የልዩነት ሀሳብ ምክንያት ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነቱ እንዲታገድና ከሀላፊነቱም ተነስቶ በአሰልጣኝነት እንዲሰራ ማድረጉን አስታውሶ ነገር ግን የልዩነት ሀሳቡን ወደ ሌላው የኢህዴን ካድሬና የሰራዊቱ አባላት ለማጋራት እያደረገው የነበረው ጠንከር ያለ እንቅስቃሴ በእጅጉ ስላሰጋው ይኸ እንቅስቃሴው እንዲገታ ለማድረግ ሲባል ታስሮ እንዲጣራ በመወሰኑ ምክንያት ይህን ውሳኔ ለማስፈጸም ህላዌ ዮሴፍና ንጉሴ ጂሞ ሀላፊነቱን እንዲወስዱ ተደረገ፡፡

ይህን የይታሰር ውሳኔን እንዲያስፈጽሙ ሀላፊነት የወሰዱት ህላዌና ንጉሴ ጂሞም ስብሰባውን ተሳትፈው ወደ ጎንደር ሲመለሱ አዲስ ዘመን ከተማ አካባቢ ይገኝ በነበረ የታጋዮች ማሰልጠኛ ማዕከል ውስጥ በሻለቃ አዛዥነት ተመድቦ ሲሰራ የነበረውን ይርጋ አበበን (ሀው ጃኖን) በአካል አግኝተው የማዕከላዊ ኮሚቴውን አዲስ የውሳኔ ሀሳብ በማስረዳት ወደ እስር ቤት ሊልኩት መሆኑን ሲነግሩት ሀው ጃኖ በባህሪው ስሜተኛና ሀይለኛ በመሆኑ ምክንያት ደግሞ ለዚህም አሰባችሁኝ በማለት ሽጉጡን ሊመዝ እጁን ወደ ወገቡ ሲዘረጋ የተመለከተው ታገይ ህላዌ በብርሀን ፍጥነት ከአካባቢው ዘወር በማለት ህይወቱን ባተረፈበት ወቅት ነው፡፡

ይህ አጋጣሚ በኢህዴን ነባር ታጋዮች ዘንድ በተዋጊነቱና በአዋጊነቱ ብቃትና ጀግንነት የሚታወቀው ታጋይ ይርጋ አበበ (ሀው ጃኖ) እና በመልካም ጸባዩና በታጋሽነቱ ይታወቅ የነበረው ንጉሴ ጂሞ መስዋዕት መሆናቸው በእጅጉ አሳዛኝ ክስተት ቢሆንም ታጋይ ህላዌ ዮሴፍ ግን ከእነዚህና መሰል የሞት አስፈሪ መንጋጋዎች በታዕምር በመትረፉ ምክንያት ለትግሉ በስኬት መደምደም የበኩሉን አስተዋጾ ከማበርከቱም በላይ ታሪክ ነጋሪና አስተማሪ የሆነ የግጥም መድብል አዘጋጅቶ በማሳተም ለንባብ እንዲያበቃ እድሉን አግኝቷል፡፡

ታጋይ ህላዌ ዮሴፍን በሚገባ እያወቅሁት የመጣሁት ዘመቻ ቴዎድሮስ ተብሎ በተሰየመውና ኢህአዴግ የማጥቃት እንቅስቃሴውን ወደ መሀል አገር ለማስፋት ሲል ጎጃምና ጎንደርን ለመቆጣጠር ቅድመ ዝግጅቱ ተጠናቆ የመጨረሻው ጥይት ከመተኮሱ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ጋይንት በተለይም መኳቢያ በምትባል የገጠር መንደር ውስጥ የህዝብ አስተዳደር ሰራተኞችን (በተለምዶ ክፍለ ህዝብ ተብለን ስንጠራ የነበርነውን ማለቴ ነው) ሰብስቦ ስለ ዘመቻው አጠቃላይ ባህሪና ከዛ በኋላ ሊከሰት ስለሚችለው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ሁኔታ እንዲሁም የሰላምና ማረጋጋት ስራው እንዴት ሊከናወን እንደሚችል ከህዝብ አስተዳደር ሰራተኞች ተግባርና ሀላፊነት ጋር በማገናዘብ ማብራሪያ ሲሰጥ ነበር፡፡

ታጋይ ህላዌ አንደበተ ርቱዕና በስሜት ውስጥ ሆኖ ሀሳቡን ከሙሉ መልዕክቱ ጋር በሚገባ ማስተላለፍ የሚችል ሰው ስለሆነ ስሜቱን ወደ ሌላው ታጋይ የማጋባት ሀይሉ እጅግ ከፍተኛ ነበር፣ ለክፍለ ህዝቦች በጊዜው ይሰጠው የነበረው ገለጻም ይህንን በስሜት የተሞላ ነገር ግን ቁምነገረኛ ባህሪውን ፍንትው አድርጎ ያሳይ እንደነበረ በሚገባ አስታውሳለሁ፡፡

ከላይ በአጭሩ ለመግለጽ እንደተሞከረው ወቅቱ ወደ መሀል አገር ዘልቆ በመግባት አዲስ አበባን ለመቆጣጠር አጠቃላይ ዝግጅት እየተደረገ የነበረበት ጊዜ ስለነበረም የህላዌ ዮሴፍ እልህና ወኔ ከአፍ እስከ ገደፉ ጢም ብሎ የሞላ እስኪመስል ድረስ ከውስጡ ፈንቅሎ በሚወጣ የጋለ ስሜትና ቁጭት እንዲሁም ጥበባዊ ለዛ ባላቸው አረፍተ ነገሮች ታጅቦ፡-

“ጓዶች እዚህ ለምን እንደተሰበሰብን በሚገባ የምታውቁ ይመስለኛል፣ ከጥቂት ቀናት በኋላ አዳዲስ ነጻ መሬቶች ይኖሩናል፣ ከእነዚህም ውስጥ ባህር ዳር፣ ጎንደርና ደብረ-ማርቆስን የመሳሰሉ ትልልቅ ከተሞች ይገኙበታል፣ እኛ የህዝብ አስተዳደር

ሰራተኞች (ክፍለ ህዝቦች) በእነዚህ በቅርቡ ነጻ በሚወጡ ከተሞች ውስጥ ገብተን በህዝቡ መሀል ስንንቀሳቀስ ደግሞ ምን አይነት ሁኔታ ሊገጥመን እንደሚችል ከወዲሁ በሚገባ መገንዘቡ ጠቃሚ ጉዳይ ነው፡፡”

በማለት ማብራሪያውን የጀመረ ሲሆን እንደተለመደው የህዝቡን ባህልና ወግ እንዲሁም እምነትና መሰረታዊ መብት አክብረን ለመንቀሳቀስ ራሳችንን ማዘጋጀት ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው ሲል ገለጻውን በመቀጠል የውይይት ሒደቱን ህይወት ሊዘራበት ይጥር ነበር፡፡ ታጋይ ህላዌ አጽንኦት ሰጥቶ ለመግለጽ እንደሞከረውም አንድ ሳምንት ባለሞላው ጊዜ ውስጥ አይቀሬው ጦርነት ተጀምሮ በሁለት ቀናት ውጊያ ብቻ ባህር ዳር ከተማና አካባቢው እንዲሁም አዲስ ዘመን ከተማና አካባቢው በኢህአዴግ ሰራዊት ቁጥጥር ስር መዋል ቻሉ፡፡

ይህንን ሁኔታ ተከትሎ ጋይንት ውስጥ በተጠንቀቅ ላይ ሆነን የሰራዊቱን የድል ዜና ብስራት እንደሰማን ወደየምድብ ቦታችን ለመንቀሳቀስ በተጠንቀቅ ላይ የነበርነው ክፍለ ህዝቦች ለሁለት በመከፈል ጉዟችንን ወደ ጎጃምና ጎንደር አደረግን፡፡ እንደ አጋጣሚ ሆኖ እኔም በታጋይ ህላዌ ዮሴፍ አስተባባሪነት ይመራ በነበረው የክፍለ ህዝቦች ቡድን ውስጥ በመመድቤ የሰላምና ማረጋጋት እንዲሁም ህዝብን የማስተዳደር ስራችንን የካቲት 19/1983 ዓ.ም ላይ ደቡብ ጎንደር አዲስ ዘመን ከተማ ውስጥ ሀ ብለን ጀመርን፡፡

ከአስር ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ማለትም የካቲት 29 ቀን 1983 ዓ.ም ጎንደር ከተማና አካባቢው በኢህአዴግ ሰራዊት ቁጥጥር ስር በመዋሉ ምክንያት ጉዟችንን ወደ ታሪካዊቷ ጎንደር ከተማ በማድረግ የሰላምና ማረጋጋት ስራችንን አጠናክረን ቀጠልንበት፡፡ የካቲት 30/1983 ዓ.ም ከጧቱ 12፡00 ስአት ጀምሮም ከህላዌ ዮሴፍ ጋር ጎንደር ከተማ ውሰጥ አብሮ የመስራት ሁኔታ ተፈጠረልኝና ታጋይ ህላዌ ዮሴፍን ይበልጥ እያወቅሁትና አርአያነቱንም እየተከተልሁ መጣሁ፡፡ አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው ከአንድ አመት ብዙም ለማይበልጥ ጊዜያት ያህል ብቻ አብረን የሰራን ቢሆንም እነዚያን አስቸጋሪ ነገር ግን ጣፋጭ የትግልና የስራ ወቅቶች ከእሱ ጋር በመስራት ማሳለፌ በእጅጉ እንደሚያኮራኝ መግለጽ እፈልጋለሁ፡፡

በዛ ላይ ጎንደር ከተማ ገብተን የሰላምና ማረጋጋት ስራችንን ሌት ተቀን በማከናወን ላይ በነበርንበት ወቅት በኢህአፓ መቺ ሀይሎች (ስኳዶች) አማካኝነት እኔና የስራ ባለደርባየን ለመግደል በማሰብ ቦንብ ተወርውሮብን ስለነበር የስራ ባለደርባየ ወዲያውኑ ሲሰዋ እኔ ግን ከፉኛ ቆስየ ነገር ግን በታዕምር ከሞት መትረፌና የህክምና እርዳታ እንደሚያስፈልገኝ ለታጋይ ህላዌ ዮሴፍ በመገናኛ ሬዲዮ ሲነገረው ይገለገልበት የነበረውን ተሽከርካሪ በአፋጣኝ ልኮ ወደ ህክምና ማዕከል እንድወሰድና ተገቢ የሆነ ህክምና እንዳገኝ በማድረጉ ምክንያት ህይወቴ ተርፋ ይኸውና እኔም እንደአቅሚቲ ታሪክ መጻፍ እንድችል ሰበብ ሆኖኛል፡፡

በአጠቃላይ በእነዚያ ፈታኝና የትግል ጽናትን አብዝተው በሚጠይቁ ነገር ግን የጎንደርን ህዝብ ሰላምና ደህንነት በማረጋገጥ ረገድ ትልቅ ቦታ በነበራቸው የአብሮነት ጊዜያት ውስጥ ከታጋይ ህላዌ ዮሴፍ በርካታ ጠቃሚ ቁም ነገሮችን ተምሬያለሁ፡፡ በተለይም ለአመኑበት አላማ እስከ መጨረሻው ድረስ ጸንቶ በመቆም መታገልን፣ ግልጽነት የተላበሰ አቀራረብ መከተልን፣ መጭውን ሁኔታ አሻግሮ የማየት ችሎታና ብቃት ማዳበርን፣ ከትግል አጋር ጋርም ሆነ ከስራ ባለደርባ ጋር ተግባብቶ መስራትንና በስርህ የሚገኘውን የሰው ሀይል አሳምኖ የማንቀሳቀስ ችሎታን እንዲሁም ህይወት ያለው ስሜትን ከውስጥ አፍልቆ በማውጣት ለሌሎች የማጋራት ሀይልን በአጠቃላይም ለህዝብ ዘላቂ ጥቅም መረጋገጥ እና ለሀገር ህልውና ሲባል ራስን አሳልፎ መስጠትን በሚገባ አስተምሮኛል፡፡ ይህንን ሀሳብ ጠቅለል ባለ መልኩ ለማስቀመጥ ያህል ስለህላዌ ዮሴፍ ማንነት፣ የአመራር ብቃትና የትግል ጽናት ከዚህም በላይ ብናገርና ብጽፍ ደስ ባለኝ ነበር፣ ሆኖም ከዚህ አጭር ጽሁፍ ዋነኛ

አላማ ጋር ብዙም ሊሄድልኝ ስለማይችል አጭር ትረካየን እዚህ ላይ ገታ ላድርገውና ትኩረቴን በእጅጉ ስቦ ይህችን ጽሁፍ እንዳዘጋጅ ምክንያት ወደሆነው የግጥም መድብሉ ዝርዝር ጉዳይ ልመለስ፡፡

በሌላ አነጋገር የዚህ ጽሁፍ ዋነኛ አላማ ታሪክና ጥበብ ብሎ በሰየመው የታጋይ ህላዌ ዮሴፍ የግጥም መድብል ላይ ያለኝን የተመጠነ አስተያየት በመሰንዘር ተደራሲያንን ለውይይት መጋበዝ ነው፡፡ ስለሆነም የዚህ መጣጥፍ አንባቢዎችም በታጋይ ህላዌ ዮሴፍ የግጥም መድብል ውስጥ የተካተቱ እጅግ አስተማሪ፣ ወኔ ቀስቃሽና ታሪክ ነጋሪ ግጥሞችን አንብባችሁ እንድታጣጥሙ ብሎም አንዳች ጠቃሚ የሆነ ትምህርት እንድታገኙበትና የራሳችሁንም አስተያየት በመሰንዘር የውይይቱ ተካፋይ እንድትሆኑ በዚህ አጋጣሚ መጋበዝ እወዳለሁ፡፡

**የግጥም መድብሉ ወቅታዊነትና የአቀራረብ ስልት**

አምባሳደር ህላዌ ዮሴፍ ታሪክና ጥበብ የግጥም መድብል በማለት የሰየመው የድርሰት ስራው በእኔ እምነት ታትሞ መውጣትና ለተደራሲያን መድረስ የነበረበት ከዛሬ ሀያ አመት ቀደም ብሎ የነበረ ቢሆንም፣ አሁንም ቢሆን ስሜቱና ለዛው እንዲሁም ማስተላለፍ የፈለገው መሰረታዊ መልዕክት ግሩም የሆነ አቀራረብና አተራረክ ይዞ በመምጣቱ ምክንያት እምብዛም ያልደበዘዘና ጊዜ ያላለፈበት ሆኖ እንዲታይ አድርጎታል ማለት ይቻላል፡፡

እኔ በበኩሌ የግጥም ስራዎችን አንብቦ በማጣጣም ረገድ ያን ያህል ጠንከር ያለ ስሜት እንዳልነበረኝ የሚታወቅ ቢሆንም ከትጥቅ ትግሉ ጊዜ ጀምሮ ለህላዌ ዮሴፍ የግጥም ስራዎች የተለየ ስሜት እየያዝሁ መምጣቴን የተገነዘብሁት ግን አምባሳደር ህላዌ ዮሴፍ እኮ የግጥም ስራዎቹን አሳትሞ በበሔራዊ ቲያትር አስመረቀ ተብሎ ሲነገር በውስጤ የተፈጠረውን ድብልቅልቅ ያለ ስሜትና መጽሀፉን አግኝቼ ለማንበብ የነበረኝን ጉጉት ሳስብ ነው፡፡

ይህም ሁኔታ ይመስለኛል የዘገየ ቢመስልም አሁን ላይ ብዕሬን አስነስቶ ከወረቀት ጋር ጣቴን ድግሞ ከኮምፒተር ጋር በማዋሀድ በግጥም ስራዎቹ ላይ ብቻ በማተኮር ሳይሆን ከላይ በመግቢያው ላይ በገለጽሁት መልኩ ታሪክን ወደ ኋላ መለስ ብየ በማስታወስ ጭምር ይህችን መጣጥፍ አዘጋጅቼ ለውይይት መነሻ ሊሆን በሚችል መልኩ ለአንባበቢያን ጀባ እንድል ያደረገኝ፡፡ የመጽሀፉ ዝግጅት ሲታይ ከተለመደው አይነት አቀራረብ ወጣ በማለት አስቀድሞ የግጥሞቹን ስሜት በስዕል መልክ ለማሳየት ከሞከረ በኋላ ወደ ግጥም ንባቡ እንድንገባ መጋበዙ ወይም ማድረጉ በራሱ ደስ የሚል ስሜትን ይሰጣል፣ ከዛም እነዛ በወኔ የተሞሉና አነቃቂ የግጥም ስኞችን አንብበን እንደጨረስን ተጨማሪ ማብራሪያዎችን በተመጠነ መልኩ ማቅረቡም የግጥሞቹን መልዕክት በትክክል እንድንረዳ ከማድረጉም በላይ በተለይም የግጥም ስንኞቹ የተጻፉበትን ጊዜ ነባራዊና ህሊናዊ ሁኔታ እንዲሁም ፖለቲካዊ ዳራ በሚገባ ለማያውቅና በአግባቡ ለመገንዘብ ለሚቸግረው ተደራሲ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ግብአት እንዲያገኝ አድርጓልና በዚህ አጋጣሚ ለታጋይ ህላዌ ዮሴፍ አበጀህ ማለት አፈልጋለሁ፡፡

ይሁን እንጂ አምባሳደር ህላዌ ለጥበብና ጥበበኞች እጅግ ቅርብ ሰው መሆኑን በመጽሀፉ መግቢያ ላይ ራሱ ከመግለጹም በላይ በታዋቂ የስነጥበብ ባለሞያዎች ከተሰጡት አስተያየቶችና ከቀረቡት የምስክርነት ሀሳቦች መገንዘብ የሚቻል ቢሆንም ከላይ በአጭሩ ለመግለጽ እንደሞከርሁት ቀደም ሲል ጀምሮ የነበረውን የጥበብ ተሰጥኦና ከጥበበኞች ጋር የፈጠረውን የተሻለ ሞያዊ ቅርበት በአግባቡ ተጠቅሞ ከዚህም በላይ ታሪክን በጥበብ አዋዝቶ በመጻፍ ለአሁኑም ሆነ ለመጭው ትውልድ በጊዜ ማስተላለፍ ሲችል ለሁለት አሰርት አመታት ያህል ዝምታን መርጦ በመቆየቱ ሳቢያ ብዙ ነገር እድናጣ ያደረገ ይመስለኛል፡፡

ምክንያቱም አንድም የግጥም ስራዎቹ የተጻፉበት ጊዜና አውድ እየራቀ እንዲሁም ነባራዊና ህሊናዊ ሁኔታውም በእጅጉ እየተለወጠ በሄደ ቁጥር የግጥም ስንኞቹ መልዕክት የማስተላለፍ ጉልበታቸው እየቀነሰ ስለሚሄድ ሁለትም እሱ ራሱም ቢሆን አንዳንዶቹን እየዘነጋቸው ወይም በመጥፋት ሳቢያ እያጣቸው ሊመጣ እንደሚችል ስለሚታወቅ በእጁ የሚገኙት ግጥሞችም ቢሆኑ ውበታቸውን ብቻ ሳይሆን የተደራሲውን ቀልብ የመሳብ ጥበባዊ አቅማቸው የዚያኑ ያህል እየቀነሰ የሚሄድበት አጋጣሚ ሊፈጠር እንደሚችል አስቀድሞ ይታወቃልና ነው፡፡

በሌላ በኩል እነዚህ የግጥም ስራዎች ከሀያ አመት በፊት ታትመው ለተደራሲያን ቢደርሱ ኖሮ ተደራሲያኑም በትኩሱ ያገኟቸው ስለነበር ሙሉ መልዕክታቸውንና ጥበባዊ ስሜታቸውን በቀላሉ ይጋሩ እንደነበር ከወዲሁ ለመገመት የሚከብድ አይሆንም፣ ምናልባትም በትጥቅ ትግሉ ወቅት እነዚህን የግጥም ስንኞች በመጠቀም በጋለ ስሜት ውስጥ ሆነው ሲዘምሩና ሲያንጎራጉሩ የነበሩ የኢህዴን ታጋዮችም ሆኑ የነባር ነጻ መሬት አርሶ አደሮች በግጥም ስራዎቹ ላይም ሆነ በቀረበው ተጨማሪ ማብብሪያ ላይ ገንቢ አስተያየት በመስጠትና ስሜታቸውን በማጋራት የራሳቸውን አዎንታዊ አስተዋጽኦ የሚያደርጉበት አጋጣሚ ይፈጠር የነበረ በመሆኑ እና በዚህም ምክንያት የግጥም መድብሉ ተደጋግሞ የመታተም እድል ያገኝ ስለነበረ ከየአቅጣጫው በሚመጡ አስተያየቶች ይበልጥ እየዳበረና የተረሱ ወይም የተዘነጉ ግጥሞችም በጊዜ የሚታወሱበትና ከየአሉበት የሚወጡበት ሁኔታ ይፈጠር ስለነበር መጽሀፉ ይበልጥ እየዳበረና እየጎለበተ የመምጣት እድሉ እጅግ ሰፊ ይሆን ነበር ብየ አምናለሁ፡፡

**የግጥም ስራዎቹ አቀማመጥን በተመለከተ**

ታጋይ ህላዌ ዮሴፍ የግጥም ስራዎቹን ቅደም ተከል አስይዞ ለማሳተም ሲያሰናዳ በሌላ ሰው ስራ ላለመጀመር በመፈለግ ይመስላል በ1969 ዓ.ም ነሀሴ ወር ላይ የጻፋቸውን ሁለት የግጥም ስንኞች አስቀድሞ ካቀረበ በኋላ በ1836 የሶሻሊዝም አስተሳሰብን ዋነኛ ቀማሪ በነበረው ካርል ማርክስ አማካኝነት ተደርሶ በ1968/9 አካባቢ ስሙ ለጊዜው ተለይቶ ባልታወቀ ጸሀፊ ወደ አማርኛ ተመልሶ በጎህ መጽሄት ላይ ታትሞ የወጣውን የግጥም ስራ አስከትሏል፡፡

ይህም ሆኖ እንደ እኔ እምነት ቅደም ተከተሉን ለማሳመር ብቻ ሳይሆን የትግሉን መጻኢ ሁኔታ ለማመላከት የካርል ማርክስ ስራ የሆነው የግጥም ስንኝ ቀዳሚውን ቦታ ቢይዝ ኖሮ ይበልጥ ስሜት ይሰጥ ነበር ብየ አምናለሁ፡፡ እንዲሁም ስለ አይበገሬው መምህር በላይነህ አርቀ አሳቢነትም ሆነ የትግል ጽናት ለመመስከርም ሆነ ስለላብ አደሩ አስከፊ የህይወት ገጽታ በመተረክ ለትግል ማነሳሳት ከተፈለገ ላብ አደሩን ከብዝበዛ ለማላቀቅ ሲባል ገዥ መደቦችን በጽናት የመታገልን አስፈላጊነት ቀምሮ እንካችሁ ያለውን ፈላስፋ መልዕክት አስቀድሞ ማቅረቡ ጠቃሚ መግቢያ ይሆን እንደነበርም በድፍረት መግለጽ እፈልጋለሁ፡፡

የግጥም ስብስቦችን ቅደም ተከተል አስይዞ የማሳተም ሁኔታ አንድም በያዙት መልዕክትና ጭብጥ ተቀራራቢነት ዙሪያ በማሰባሰብ አሊያም በተጻፉበት ቀን፣ ወርና ዓ.ም ቅደም ተከተል ላይ ተመስርቶ ሊሆን እንደሚችል ለሙያው ቅርበት ያላቸው ሰዎች ሀሳባቸውን ሲገልጹ ይደመጣሉ፣ ከዚህ አንጻር የታጋይ ህላዌ ዮሴፍ የግጥም ስንኞች ቅደም ተከተላዊ አቀማመጥን ስንመለከት በአብዛኛው የተጻፉበትን ቀን፣ ወርና ዓ.ምን መሰረት አድርገው የቀረቡ ቢመስልም አንዳንድ ጊዜ የወጣ ገባነት ሁኔታ በግልጽ ተስተውሎባቸዋል፡፡

ለምሳሌ ጥሪየ ጥቅምት 22/1973 ዓ.ም እንዲሁም ቀይዋ እኾኽ በሚል ርዕስ የካቲት 1973 ዓ.ም ላይ የተጻፉት የግጥም ስንኞች እያሉ ምንም አይነት የተለየ አሳማኝ ምክንያት ሳይቀመጥ ከወራት በኋላ ማለትም መጋቢት 1973 ዓ.ም የተጻፈውና ማለዳ ነው ጊዜው የሚል ርዕስ የተሰጠው የግጥም ስንኝ በመጽሀፉ ውስጥ ቅድሚያ ተሰጥቶት እናገኘዋለን፡፡

ወደ ሌሎች የመጽሀፉ ገጾች እልፍ ብለን ስንመለከትም በ1975 ዓ.ም የተጻፈውና ሌላ ምን ደስታ አለ?... ከመታገል በቀር፣ የሚል ርዕስ የተሰጠው የግጥም ስንኝ በ1976 ዓ.ም ከተደረሰውና ኢህዴን አበራች ከሚለው የግጥም ስንኝ በኋላ ባሉት ገጾች ውስጥ ተቀምጦ እናገኛለን፡፡ የዚህ አይነት የቅደም ተከተል መዛባቶች በተለይም በ1975 እና በ1976 ዓ.ም በተጻፉት የግጥም ስንኞች ላይ ተደጋግሞ ታይቷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በአንድ ወይም በሁለት ቦታ ላይ ብቻ የተከሰተ ቢሆንም የስዕሎች ቦታ መቀያየር ወይም ያለቦታቸው መገኘታቸው የሚፈጥረው ግርታም ግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል፣ በዚህ ረገድ በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችለው የታጋይ ሙሉ አለም አበበን የትግል ሒደት ለማሳየት የተጠቀመበት ምስል በሌላ የግጥ ስንኝ ላይ መገኘቱ ነው፡፡ ይህም ሆኖ በመሰረታዊ የሀሳብ ጭብጡና ማስተላለፍ በተፈለገው መልዕክት ላይ የፈጠረው የጎላ ችግርም ሆነ መደናገር አለ ብየ አላምንም፡፡

ሆኖም በቀጣይ መጽሀፉ እንደገና የሚታተምበት ወይም ተሻሽሎ ለህትምት የሚበቃበት አጋጣሚ የሚፈጠር ከሆነ ታጋይ ህላዌ ይኸንን በቅደም ተከተል አቀማመጥ ላይ የተስተዋለውን ክፍተት ለማረም ጥረት እንዲያደርግ በዚህ አጋጣሚ ማስገንዘብ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ በሌላ አነጋገር እነዚህንና መሰል ጉድለቶችን አርሞና ሌሎችንም ጠቃሚ ሀሳቦች ጨምሮበት የግጥም መድብሉን እንደገና ቢያሳትመው ለተደራሲያንም ሆነ ለባለታሪኮቹ የተሻለ ሁኔታ ሊፈጠርላቸው ይችላል የሚል እምነት አለኝ፡፡

**ማጠቃለያ**

ታጋይ ህላዌ ዮሴፍን እጅግ በጣም ጥሩ ተራኪና ገጣሚ ነው የሚለው አረፍተ ነገር ብቻ በአግባቡ የሚገልጸው አይመስለኝም፣ ይልቁንም ራሱ ህላዌ ጥሩ ትርክትና ግጥም ነው ቢባል ትክክለኛውን ህላዌ ዮሴፍን ይገልጸው እንደሆነ አላውቅም፡፡ ታጋይ ህላዌ ግጥም መጻፍ ብቻ ሳይሆን ታሪክን በአግባቡ እየተረከ መሰነድም እንደሚችል በዚህ የግጥም መድብል መግቢያ ላይ ያሰፈረውንና ከግጥም መድብሎች አንጻር ሲታይ ረዘም ያለ ታሪክ ነጋሪ የማብራሪያ ሀሳብ በማንበብ ብቻ ይህንን እምቅ ችሎታውንና የመተረክ ተሰጥኦውን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ለማንሳት እገደዳለሁ፣ የኢህዴን-ብአዴን ታሪክ ከ1973-2008 በሚል ርዕስ የተወሰኑ የብአዴን ከፍተኛ አመራሮች ጽፈው ያሳተሙት መጽሀፍ አዘጋጆች ለምን ይሆን የታጋይ ህላዌ ዮሴፍን መጽሀፍ በማጣቀሻነት ሳይጠቀሙበት የቀሩት? የሚል፣ ለነገሩ እንዳው ነገርን ነገር ካነሳው ብየ እንጂ እነሱ እንደሆኑ የመጽሀፉ ጥራት፣ ምሉዕነትና ተነባቢነት መቼ ያን ያህል ያስቸንቃቸውና፡፡ የዚህን መደምደሚያ እውነትነት ለማረጋገጥ የፈለገ ሰው በዚሁ መጽሀፍ ላይ ቀደም ብየ የሰጠሁትን ግምገማዊ አስተያት በአይጋ ፎረም ድረገጽና በእኔ የፌስ ቡክ ገጽ ላይ አግኝቶ እንዲያነብ ይመከራል፡፡

በእርግጥም የኢህዴን ትክክለኛ የትግል ታሪክ በአግባቡ መጻፍ ካለበት ታምራት ላይኔን ጨምሮ በታጋይ ህላዌ ዮሴፍ፣ መዝሙር ፈንቴና መሰል ጓዶቻቸው የግጥም ስንኞች እየተዋዛና ከባቢያዊ ሁኔታውም በሚገባ እየተብራራ መሆን አለበት ብየ

አምናለሁ፡፡ በመጨረሻም ምንም እንኳ የታጋይ ህላዌ ዮሴፍን የግጥም ስንኞች በአብዛኛው የምወዳቸው ቢሆንም የተወሰኑት ግን በእጅጉ ቀልቤን ሰቅዘው በመያዝ ግጥም የማንበብ ፍላጎቴን እንድፈትሽ አድርገውኛል ማለት እችላለሁ፡፡

እነዚህም የግጥም ስንኞች በዋነኛነት የሚከተሉት ናቸው፣ ለታጋይ ስመኝ ምናለ (የትግል ስሟ ድላይ) የተገጠመው እኔም እንደ አንቺ ድል ላይ ልቁም ከአሳማኝ ማብራሪያው ጋር ከገጽ 51 ጀምሮ፣ ያልተንበረከከነው ገጽ 98፣ ደማቅ ታሪክ ጻፈ ገጽ 145፣ የምስራች ይበሉሽ ከአሳዛኝ ትርክቱ አንጻር ሲታይ ከገጽ 259 ጀምሮ እና እንደሞላች ትኑር እንጂ የታጋይ ሙሉ አለም አበበን የትግል ጽናት፣ ተግባቢነትና ተወዳጅነት የገለጸበት ከገጽ 276 ጀምሮ ባሉት ገጾች ላይ የሰፈሩት የግጥም ስንኞች በአንድ በኩል የትግል ጽናትንና የጀግንነትን ወኔ የሚያላብሱ፣ በሌላ በኩል የሀዘንንና የቁጭትን ስሜት በማጋራት አንጀትን ያላውሳሉና፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የታጋይ ህላዌ የግጥም ስራዎች የደራሲውን ምናባዊ ፈጠራ ምጥቀትና አስቀድሞ የመተንበይ ችሎታን በግልጽ የሚያሳዩ ከመሆኑም በላይ በትግል ጽናት ላይ ያለውን የማያወላዳ አቋም ይበልጥ ያረጋግጣሉ፣ ስለሆነም እኛም የግጥም ስንኞቹን ከነ ማብራሪያቸው አንብበን እንድናበረታታው ቢደረግ፣ እሱም ይኸን ወጣ ገባ የማለት ሁኔታውን ወዲያ አሽቀንጥሮ በመጣል እንደ ወትሮው ሁሉ አሁንም በወቅታዊው የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ መጻፉን ቀጥሎበት ሁለተኛውን የታሪክና ጥበብ መጽሀፍ ጀባ እንዲለን እየተመኘሁ ሌሎች ታጋዮችም የእሱን አርአያነት ሊከተሉ ይገባል እላለሁ፡፡